# ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የድጋፍ ድርጅት
## በስዊዘርላንድ
KINIJIT UNTERSTÜTZUNGSORGANIZATION IN DER SCHWEIZ

**Postfach 1124, 8152 Opfikon - Switzerland**

***<u>በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ሚሊኒየምን ለማክበር የቀረበ ጥሪ</u>***

*አምባገነንና ኢዲሞክራሲያዊ መንግስታት ባደረሱብን አፈናና ጭቆና ሳቢያ ከምንወዳትና ከ
ምንሳሳላት ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ባህር ማዶ ተሻግረን በተቀሩት የአለማችን ማእዘናት
ተበታትነን የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በምንገኝበት ቦታ ሁሉ አሮጌውን ሚሊኒየም ለመሸኘት
፤ አዲሱንና መጪውን ደግሞ የእድገትና የብልፅግና መልካም ዘመን እንዲሆንልን በመመ
ኘትና ለዚህም ምኞት እውን መሆን የበኩላችንን ድርሻ በተግባር ለመወጣት እንድንችል በ
ተደጋጋሚ ባዘጋጀናቸው የውይይት መድረኮች ተመካክረን በእግዚአብሄር ፈቃድ ዛሬ የበእ
ሉን አከባበር መርሃ ግብር ወደመተግበሩ ወሳኝ ምእራፍ ተሸጋግረናል።*

*በዚህ መሰረት የዚሁ አለምአቀፍ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች አንዱ አካል የሆንን እኛ በስዊ
ዘርላንድ የምንኖር ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች አዲሱን ሚሊኒየም እዚህ በምን
ኖርበት አገር በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ወሰነናል።*

*የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ክብረ በአል ዝግጅት ለዚህ ወይም ለዚያ የፖለቲካ ድርጅት፣ ማህ
በር ወይም ግለሰብ ብቻ የሚተው የግል ጉዳይ እንዳልሆነ በስዊዘርላንድ የቅንጅት ለአንድነ
ትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ድርጅት በፅኑ ያምናል። አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንና የ
ሲቪክ ማህበራት ተጠሪዎች፣ የተቃዋሚ ፓለቲካ ድርጅት አባላት በአንድነት ቆመን ይህን
በአል እንድናዘጋጅና በመቀጠልም በጋራ እንድናከብር የድጋፍ ድርጅቱ በታላቅ አክብሮት
ጥሪውን ሲያስተላልፍ ከልብ በመነጨ ስሜት ነው።*

*ይህ አገራዊ ጥሪ በደብዳቤ ወይም በድህረ ገፃችን በኩል የቀረበላችሁ ድርጅቶችና ግለሰቦ
ች በአጠቃላይ በተጠቀሰው የድጋፍ ድርጅት በኢሜል ወይም በፖስታ አድራሻ የበኩላችሁ
ን ምላሽ በአስቸኳይ እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን።*

***እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ***
***ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ***

***ኤፕሪል*** *23, 2007*
***በስዊዝ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት***

**KINIJIT Support organization in Switzerland**
**Postfach 1124 , 8152 Opfikon**
**SWITZERLAND**
kinijitch@yahoo.com